# ለሐዋርያ ዓዉደ-ሃሳብ ዓምድ፤

ክቡራትና ክቡራን፣

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁንና አሥተያየታችሁን ትልኩልን ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን፡

ጥያቄ1፡ መጭውን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ በመሳተፍና ባለመሳተፍ ጠርዝ የተወጠረ ጥያቄ ተነስቱዋል; ለሕዝባዊው ዴሞክራሲያዊ ትግልም ሆነ ለተቃዋሚዎች ግንባር ቀደም ሚና የትኛው አካሄድ ይበጃል ይላሉ? ለምን?

ጥያቄ2፡ ምርጫውን አስመልክቶ እስካሁን በተካሄደው ሂደት ምን ታዝበዋል? አካሄዱ አፈጻጸሙን አመላክቱዋል ይላሉ? ግምገማዎንና ትዝብትዎን በመረጃ አስደግፈው ለአንባቢዎቻችን ቢያብራሩልን?

ጥያቄ3፡ በኢትዮጵያችን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ክንዋኔዎች የሴቶችን ጉልህ ተሳትፎ የሚጠራ ቀላይ ድምጽ አለ። ሴቶች እህቶቻችንና እናቶቻችን በተፈለገው መጠን በተሳትፎ ላይ ተሰማርተዋል ይላሉ? ለምን/እንዴት?

ጥያቄ4፡ በያመቱ ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ይታሰባል። የዘንድሮውን ካምናው የለየው/የሚለየው ምን ይሆን? የሴቶችን የመብትና የእኩልነት ትግል እያንዳንዱ ሰው እንዴት ሊያግዝ ይችላል?

ጥያቄ5፡ በዚህ ዓመት ግንቦት ወር ውስጥ ለሚካሄደው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ምን ይጠበቃል? ለመንግሥታትና መንግሥታት ላልሆኑ ዓለም አቀፍ አካሎች ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?

ጥያቄ6፡ ባለፈው የዓዉደ- ሃሳብ አቅርቦቶች ላይ ገንቢው አስተያየትዎ ምን ይመስላል? በየፈርጁ የሚጨምሩት፡ የሚነቅፉት፡ ቢሻሻል የሚሉትና የሚያዳብሩት ጉዳይ ካለ እባክዎ ይሳተፉና የበኩልዎን አስተዋጻኦ ያበርክቱ?

//////////////////////////////// ……./////////////////////////////

ማስታወሻ፡ ለነዚህ ጥያቄዎችም ሆነ በእርስዎ ግምት መካተት አለባቸው ለሚሉዋቸው ሌሎች ጥያቄዎች መልስዎትንና አስተያየትዎን ከማርች 10/2010 በፊት እንዲልኩልን በትህትና እናሳስባለን።

የመላኪያ መንገድ፡ hawarya.publications@sympatico.ca ይሁን።

ለሚደረግልን ትብብር በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን

ከሐዋርያ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል

EthioLion.Com